የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 36
ADDIS ABABA - 29th June, 2001

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፭/፲፱፻፺፫ ዓ·ም· ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግን ሥርዓት ተፈጻሚነት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፩ሺ፭፻፵፬

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 75/2001
Tax Withholding Scheme Application Council of Ministers Regulations ........................ Page 1544

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፭/፲፱፻፺፫ ዓ·ም ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግን ሥርዓት ተፈፃሚነት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና ከማናቸውም ገቢ ግብር ለማስከፈል በወጣው (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፯/፲፱፻፺፫ አንቀጽ ፵ (ሐ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግን ሥርዓት ተፈጻሚነት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፸፭/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ግብር ከፋዮች

ደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ፣ የሕግ ሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ የመንግሥት መ/ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶችና ዕቃዎች ለሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች ከሚፈፅሙት ማናቸውም ክፍያ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፵ (ሐ) መሠረት ፭ ፐርሰንት (አምስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው ያስቀራሉ፡

፩· ከምክር አገልግሎት፡

፪· ከዲዛይን ሥራዎች ፣ ከፅሑፎች ፣ ከትምህርት ገለፃዎች እና መረጃን ከማሠራጨት ሥራዎች፡

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 75/2001*

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE APPLICATION OF TAX WITHHOLDING SCHEME*

These Regulations are issused by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 40(c) of the Income Tax (Amendment) Proclamation No. 227/2001.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Tax Withholding Scheme Application Council of Ministers Regulations No. 75/2001".

2. *Tax Payers to Which the Withholding Scheme is Applied*

Category "A" taxpayers, organizations having jurdical personality, government agencies, private non profit institutions, and non-governmental organizations shall, pursuant to Article 40(c) of the Proclamation, withhold income tax of 5% from payements they make to tax payers providing the following services and goods:

1) Consultancy service;

2) Designs, written materials, lectures and dis-semination of information;

፫. ከጠበቆች ፡ ከሂሳብ ባለሙያዎች፣ ከኦዲተሮች እና ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ከሚሰጡ ሰዎችና ድርጅቶች፣
፬. ሺያጭ ከሚያከናውኑ ሠራተኞች ፡ የአገልግሎት ክፍያ ሰብሳቢዎች ፡ ፕሮፌሽናል የኪነ ጥበብና የስፖርት ባለሙያዎች ፤ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሻጮችን ጨምሮ ከማንኛውም ደላላ እና ሌሎችም የኮሚሽን ወኪሎች፣
፭. በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ከሚተላለፉ ማስታወቂያዎች እና የመዝናኛ ዝግጅቶች፣
፮. ለሥራ ተቋራጮች ከሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ፣
፯. ከማስታወቂያ አገልግሎት፣
፰. ከሳይንስ ግኝቶች እና የፈጠራ ውጤቶች ባለመብትነት፣
፱. ኮምፒውተሮችን ጨምሮ ፡ ከተለያዩ መሣሪያዎች፣ ሕንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ፣
፲. ከጥገና አገልግሎት፣
፲፩. በአንድ ጊዜ ግዥ ከብር ፲ ሺ. በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት ከሚፈፀም ክፍያ።

፫. ግብሩን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው ወይም ድርጅት ግዴታ

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪ ለተዘረዘሩት አገልግሎቶችና ዕቃዎች ከሚፈፀም ክፍያ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው ወይም ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

፩. ግብር ለተቀነሰበት ሰው ወይም ድርጅት ተከታታይ ቁጥር ያለው ሕጋዊ ደረሰኝ ይሰጣል።
፪. ክፍያ የተፈፀመለትን የእያንዳንዱን ሰው ወይም ድርጅት ስም እና የሥራ አድራሻ ፡ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ፡ (የተሰጠ ከሆነ) በወሩ ውስጥ ለተጠቀሰው ሰው ወይም ድርጅት የተከፈለውን ገንዘብ አጠቃላይ ድምር ፡ ተቀናሽ የተደረገውን ግብር ልክ ፡ በየወሩ ከግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚሰጠው ቅጽ ሞልቶ ያቀርባል።
፫. በወሩ ውስጥ ከተከፈሉ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተመለከተው ቅጽ ጋር ለግብሩ ባለሥልጣን ገቢ ያደርጋል።

፬. የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ግዴታ

የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን፣

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፪) የተመለከተውን ቅጽ አዘጋጅቶ ያሠራጫል።
፪. ከክልል የግብር አስገቢ ባለሥልጣኖች የሚደርሰውን መረጃ መሠረት በማድረግ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረግባቸውን የሥራ ዘርፎች ዝርዝር ያሻሽላል።

፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር



3) Lawyers, accountants, auditors, and other services of similar nature;
4) Sales persons, service fee collectors, arts and sports professionals, entertainers, any broker including insurance brokers and other commission agents;
5) Advertisements and entertainment programs for television and radio broadcasts;
6) Construction services;
7) Advertisement services;
8) Patents for scientific and intellectual works;
9) Rent or lease of equipments including computers, buildings and other goods;
10) Maintenance services;
11) Supply of goods involving more than Birr 10,000 in any one transaction.

3. *Obligations of Withholding Agents*

Any person or organization who, by law, is required to withhold tax from persons and organizations supplying the services and goods listed under Article 2 above shall have the following obligations:

1) issue serially numbered official receipt to persons and organizations from whom tax is withheld;
2) fill in a form to be supplied by the revenue authority the name, tax payer identification number (if such TIN is supplied) of a person, or organization to whom payment is made, and the total amount of money paid and tax withheld;
3) Person and organization withholding the tax shall transfer to the revenue authority the amount withheld within the month, together with the form indicated under sub-Article (2) above.

4. *Obligations of the Federal Inland Revenue Authority*

The Federal Inland Authority shall:

1) Prepare and distribute the form mentioned under Article 3(2) above.
2) On the basis of information received from regional tax authorities, increase the list of services and goods from which tax shall be withheld.

5. *Effective Date*

These Regulations shall come into force as of the 8th day of July 2001.

Done at Addis Ababa, this 29th day of June, 2001.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE